ንን ይተዋወቁ

# Maryland Health Connection

Maryland Health Connection በሜሪላንድ ውስጥ የጤና መድህን ግብይት የሚፈጸምበት ቦታ ነው። **MarylandHealthConnection.gov** በሚለው ድረ-ገጽ ላይ የጤና እቅዶችንና ዋጋቸውን ማነጻፀር ብሎም እርስዎና ቤተሰብዎ ጥራት ያለው የጤናና የጥርስ ህክምና መድህን ሽፋን ማግኘት ይችላሉ።

## የመድህን ሽፋን የሚሰጣቸው አገልግሎቶች

ሁሉም የጤና እቅዶች እንደሚከተሉት ላሉ ወሳኝ ጥቅማ ጥቅሞች የመድህን ሽፋን ይሰጣሉ:-

- የሀኪም ቀጠሮዎች
- ሆስፒታል ገብቶ መታከም
- የድንገተኛ ህክምና
- በሃኪም የሚታዘዙ መድሀኒቶች
- የአእምሮ ጤና ህክምና
- የእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ህክምና
- የህጻናት ህክምና
- የላቦራቶሪ ምርመራዎች
- የአደንዛዥ መድሃኒቶች ሱሰኝነት ህክምና
- ስር የሰደዱ ህመሞች ህክምና
- የመከላከልና የእንክብካቤ ህክምና (እንደ ክትባት፣ የደህንነት እና ቅድመ ምርመራ)

## ቁጠባዎች

ባለፈው ዓመት ከተመዘገቡት ከ10 የሜሪላንድ ነዋሪዎች ውስጥ ዘጠኙ የጤና እቅዳቸውን ለመሸፈን የሚያስችላቸውን የገንዘብ ድጋፍ አግንተዋል። እነዚህ ቁጠባዎች የሚሰሉት በቤተሰቡ ገቢና ብዛት መሰረት ነው። በMaryland Health Connection በኩል ሊያገኙዋቸው የሚችሏቸው ጥቅሞች:-

- በግል የጤና መድህን ዕቅድ አማካይነት ወርሃዊ ክፍያዎን የሚቀንሱ የግብር ዱቤዎች።
- **Medicaid** ወይም በ**Maryland Children's Health Program** ነጻ ወይም ዝቅተኛ ክፍያ።

## ምዝገባን የሚመለከት እገዛ

የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በመጠቀም ያለ ክፍያ በግለሰብ ደረጃ እገዛ እንሰጣለን። እያንዳንዱ የሜሪላንድ ካውንቲ፣ የጤና እቅድ በማግኘት ረገድ ያሉዎትን ማናቸውንም ጥያቄዎች ለመጠየቅና ለመመዝገብ የሚያስችሉዎ ቢሮዎች አሏቸው። በአቅራቢያዎ የሚገኘውን ቢሮ ለማግኘት MarylandHealthConnection.gov/help የሚለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ።

በተጨማሪም **1-855-642-8572** ላይ መደወል ይችላሉ **(**መስማት የተሳናቸውና የመስማት ችግር ያለባቸው **(Relay)** መጠቀም ይችላሉ**)**። ቋንቋዎን የሚናገር የጤና መድህን ባለሙያን በቀላሉ በስልክ ማግኘት ይችላሉ።

በግል የጤና መድህን ለመመዝገብ፣ ከኖቬምበር 1 እስከ ዲሴምበር 15 ባሉት "ለምዝገባ ክፍት" በሆኑ ጊዜያት በMarylandHealthConnection.gov ላይ ወይም Enroll MHC የተባለውን ነጻ የተንቀሳቃሽ ስልክ መተግበሪያችንን በመጠቀም መመዝገብ ይኖርብዎታል። ብቃቱን የሚያሟሉ ከሆነ በዓመቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ለMedicaid መመዝገብ የሚችሉ ሲሆን ጊዜው ሲደርስ ሽፋንዎን እንዲያድሱ ይነገርዎታል።

በህይወትዎ ትልቅ ዋጋ የሚሰጡት ሁኔታ ካጋጠመዎ ማለትም ጋብቻ ከፈጸሙ፣ ወደ ሜሪላንድ ከተዛወሩ፣ ከስራ ከወጡ ወይም 26 አመት ከሞላዎና በወላጆችዎ ስር የሚያገኙትን የመድህን ሽፋን ካጡ፣ መመዝገብ ይችሉ ይሆናል። አብዛኛውን ጊዜ፣ ልዩ የመመዝገቢያ ወቅትን ተጠቅመው ለአዲስ የጤና ሽፋን ለመመዝገብ 60 ቀናት ይኖርዎታል።

@MarylandConnect

© 2022 Maryland Health Benefit Exchange | MHC050_052022_AM